የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፱
አዲስ አበባ ኅዳር ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፪

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

6th Year No. 9
ADDIS ABABA - 2nd December, 1999

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩፻፹፯/፲፱፻፺፪ ዓ.ም.
የኢትዮጵያን የምርጫ ሕግ ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ጋር ለማጣጣም የወጣው (ማሻሻያ) አዋጅ ...................................... ገጽ ፩ሺ፩፻፹፬

## CONTENTS

Proclamation No. 187/1999
A proclamation to make the Electoral Law of Ethiopia Conform with the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia (Amendment) Proclamation ........................................... Page 1184

### አዋጅ ቁጥር ፩፻፹፯/፲፱፻፺፪
### የኢትዮጵያን የምርጫ ሕግ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

በመንግሥት ሥራ ላይ የተሰማሩ ዜጎችን በምርጫ ተወዳዳሪነት የመሳተፍ ዕድል ለማስፋት፣ የኢትዮጵያን የምርጫ ህግ አዋጅ ከሕገመንግሥቱ ጋር ለማጣጣም የወጣውን አዋጅ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) (መ) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>
ይህ አዋጅ «የኢትዮጵያን የምርጫ ሕግ አዋጅ ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት ጋር ለማጣጣም የወጣው (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፩፻፹፯/፲፱፻፺፪» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· <u>ማሻሻያ</u>
የኢትዮጵያን የምርጫ ሕግ አዋጅ ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት ጋር ለማጣጣም የወጣው አዋጅ ቁጥር ፩፻፲፩/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፵፮ እንደሚከተለው ተሻሽሏል።
፩· ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሠርዟል፤
፪· የቀድሞዎቹ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) ቁጥራቸው ተስተካክሎ እንደቅደም ተከተላቸው ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ሆነዋል።

፫· በንዑስ አንቀጽ (፩) መጀመሪያ ላይ «በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሱት» የሚለው ሐረግ ተሠርዟል።

፬· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>
ይህ አዋጅ ከህዳር ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ·ም· ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ህዳር ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ·ም·

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

### PROCLAMATION NO.187/1999
### A PROCLAMATION TO AMEND THE ELECTORAL LAW OF ETHIOPIA PROCLAMATION

WHEREAS, it is found necessary to amend the proclamation to make the Electoral Law of Ethiopia conform with the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, with a view to enhancing the opportunity to stand for election in respect of citizens engaged in government employment;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (2) (d) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. Short Title
This Proclamation may be cited as the 'Proclamation to make the Electoral Law of Ethiopia conform with the constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia (Amendment) Proclamation No. 187/1999.

2. Amendment
Article 46 of the Proclamation to make the Electoral law of Ethiopia conform with the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, Proclamation No. 111/1995, is amended as follows:
1) Sub-Article (1) is deleted;
2) The previous Sub-Articles (2) and (3) are renumbered as Sub-Articles (1) and (2) respectively.

3. The phrase ''referred to in Sub-Article (1) of this Article'', appearing at the beginning of Sub-Article (1), is deleted.

4. Effective Date
This Proclamation shall enter into force as of the 2nd day of December, 1999.

Done at Addis Ababa, this 2nd day of December, 1999.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REUBLIC OF ETHIOPIA

ያንዱ ዋጋ 2·30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001